**ሴቶችን ጅብ አስበልቶ እንደ ወንድ ችግኝ ተከላ!**



ሱሪ ቦላሌ ሆነና ቀበቶ ላልቶ በጦቢያ፣
እንደ ምስጥ አፈር ይምሳል አንጠልጥያለሁ ባይ ሁላ፣
ሴቶችን ጅብ አስበልቶ እንደ ወንድ ችግኝ ተከላ፡፡

የግዮን ፉፏቴ ሲደርቅ ጣና ሀይቅ ሲሆን ሰሃራ፣
እንደ እባብ ሲንፏቀቅ ዋለ የማይጸድቅ በለስ ተከላ!

ምሁር ነኝ ባዩ ዶክተሩ የነፍሰ-ገዳይ ቱልቱላ፣
የግድብ ጠልሰም ይጨራል እምቦጭ ሲነግስ በጣና፡፡

ኢትዮጵያ እንድትሆን ኤደንን፣ መቀነት ታጥቃ ግዮንን፣
በላ ትከላ ፍትህን፣ ቅጥፈትን ነቅለህ እውነትን!

ችግኝ ተተክሎ እንዲበቅል፣ ፀድቆ አገፍግፎ እንዲያብብ፣
ይልቅስ እውነት ተናገር፣ ንስሃ ግባ ለወንጌል፡፡

በሰእማት አጥንት ፍርስራሽ፣ ከንፁሐን ደም መስኖ ቅጅ፣
ችግኝ ተከላ ተማወጅ፣ ቅድሚያ እጅ ታጠብ ቀላማጅ፣
ተአቡነ ጴጥሮስ ተደፍተህ፣ ንስሃ ግባ ባማላጅ፡፡

ለሃያ ዓመታት እንደ ደን፣ ሕዝብ በባሩድ ጨፍጭፎ፣
አፈሩን በደም ለውሶ፣ በአጥንት አማስሎ አቡክቶ፣
አረም ዘራበት አፍልሶ፣ ተጀግኖች አገር ሰው ጠፍቶ፡፡

በጋሞ ልጆች ደም አምባ፣ በጌዶ እናቶች ልቅሶ እንባ፣

በሰበታዎች ነፍሰ-ጡር፣ በለገጣፎ እርጉዝ ጽንስ ውሀ፣
ምድር አርጥቦ ቆፈረ፣ ሽፍጥ እንደ ጉንዳን አፈላ!

በወልቃይት ምድር አበሳ፣ በራያ መሬት ጠባሳ፣
በደራ ጋራ ሰቆቃ፣ በመተከል ወንዝ መከራ፣
የችግኝ ሥሮች ሰደዳ፣ አቤት ህሊናን ሲያደማ!

በፃድቃን ገላ ተተክሎ፣ የሰማእት ደም ጠጥቶ፣
እንዴት ሥር ሰዶ ይፀድቃል፣ ችግኝ በይሁዳ ተተክሎ?

ትናንት በመርዝ ሱስ አፍዞ፣ ዛሬም በችግኝ ሽፍኖ፣
ገደል መክተቱን ቀጥሏል፣ በሬውን በሳር አታሎ፡፡

ይልቅስ ትተህ ቅፈላ፣ መንጋን ማድረጉን ተላላ፣
ቀኑ ደማምኖ ሳይጨልም፣ በጊዜ ንስሃ ግባ!

በደም በተበከሉ ጣቶች ችግኝ መትከሉን ተውና፣
ይልቅስ ሴቶቹን አትርፍ ተጅብ መንጋጋ አውጣና፡፡

ግድብ ግደባ ተመንጉድ በፊት መተከል ተካርቱም ተራ፣
ምንጩን ተመድረቅ አትርፍ ዘመቻ ጣና ጥራና!

ችግኞች መትከል ታማረህ፣ የፅድቅ የምረት ንስሃ!
ወንጀልህን በሱባኤ እጠብ፣ ዋልድባ ገዳም ግባና፡፡

እውነት ተበቃህ ኃጥያትህ፣ ልብህ ታሰበ ንስሃ፣
ተንኮል ክፋትን ለማልበስ፣ አፈር መጫሩን ተውና፣
የእውነትን ፍሬ አፍልተህ፣ የፍትህ ችግኝ ትከላ!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
መጀመርያ ሐምሌ ሁለት ሺ አስራ አንድ ዓ.ም.
እንደገና ነሐሴ ሁለት ሺ አስራ ሁለት ዓ.ም.